

ስደተኞች ማን ናቸው?

የ 1951 የስደተኞች ስምምነት እንደሚለው ስደተኛ ማለት...

“በዘር፣ በሃይማኖት፣ በዜግነት፣ በተወሰነ የማህበረሰብ ወይም የፖለቲካ ቡድን ውስጥ አባል በመሆን የተነሳ በእውነታ ላይ በተመሰረተ የመከሰስ ፍርሃት ከገዛ አገሩ የወጣ፣ እናም በዛ አገር ጥበቃ ውስጥ ለመጠለል ያልቻለ፣ ወይም ከፍራቻ የተነሳ ፍቃደኛ ያልሆነ” ማለት ነው።

## ጥቅማ ጥቅሞች ለማግኘት ወዴት ልሂድ?

ቦልቲሞር ከተማ ኮሚኒቲ ኮሌጅ **
ቦልቲሞር....................................................410-986-5464

ቦልቲሞር የከንቲባው የስራ ማጎልበቻ ቢሮ
ቦልቲሞር....................................................410-396-3009

የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ማጎልበቻ ካውንስል*$
ሲልቨር ስፕሪንግ........................................... 301-562-7301

ኢንተርናሽናል ሬስኪው ኮሚቴ*$
ቦልቲሞር ....................................................410-327-1885

ኢንተርናሽናል ሬስኪው ኮሚቴ*$
ሲልቨር ስፕሪንግ...........................................301-562-8633

የአይሁድ ማህበረሰብ አገልግሎቶች*$
ቦልቲሞር....................................................443-451-2256

የናሽናል ካፒታል አካባቢ የሉተራን የህብረተሰብ አገልግሎቶች*$
ሃያተስቪል..................................................240-714-4034

የሜሪላንድ የጤና እና የአእምሮ ጤና ዲፓርትመንት
ቦልቲሞር.................................................... 410-767-6664

የሜሪላንድ የስደተኞች እና ጥገኝነት ቢሮ
ቦልቲሞር.................................................... 410-767-7514

ሞንትጎመሪ ካውንቲ ኮሚኒቲ ኮሌጅ**
ሲልቨር ስፕሪንግ. .......................................... 240-567-1409

ፕሪንስ ጆርጅ ኮሚኒቲ ኮሌጅ**
ሃያተስቪል ............................................... 301-546-8449

ወርልድ ሪሊፍ*$
አኔ ሩንዴል................................................ 410-760-4514

* የአካባቢ የስደተኛ መልሶ ማስፈሪያ ኤጀንሲን ያመለክታል
** እንግሊዝኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የት እንደሚማሩ ያመለክታል
$ አርቲሲኤ ለማግኘት የት እንደሚያመለክቱ ያመለክታል

Maryland’s Human Services Agency



# ኤምኦአርኤ

## የሜሪላንድ የስደተኞች እና ጥገኝነት ቢሮ

ወደ የአሜሪካ ማህበረሰብ መቀላቀላቸውን ለማገዝ እና ለማቅለል በፌዴራል ደረጃ ለታወቁ ስደተኞች እና ፖለቲካ ጥገኞች ድጋፍ እና አገልግሎቶችን እናቀርባለን።

ለጠቅላላ ጥያቄዎች ኤምኦአርኤን በ 410-767-7514 ያግኙ።

Maryland’s Human Services Agency



ኤምኦአርኤ ከ 40,000 በላይ ለሆኑ ስደተኞች ሜሪላንድን ቤታቸው እንዲያደርጉ ረድቷል፤ ከ”ተፈናቃይ ሰዎች” ወደነጻ፣ ለብሄራዊ ምጣኔ ሃብት እና ለአካባቢው ማህበረሰብ አበርካች ሰዎች እንዲሸጋገሩ አግዟል። ስደተኞች በተቻለ ፍጥነት እራሳቸውን እንዲችሉ ለመርዳት ባለመ መልኩ የተዘጋጁ የመሸጋገሪያ አገልግሎቶችን በማቀድ፣ በመምራት እና በማቀናጀት ከተለያዩ የህዝባዊ እና የግል አገልግሎት አቅራቢዎች ጋር ይሰራል። ስደተኞች ወደ አሜሪካ ህይወት እንዲሸጋገሩ የሚረዱ ቁልፍ ቦታዎች የሚያጠቃልሉት የገንዘብ እርዳታ፣

## ለኤምኦአርኤ አገልግሎቶች ማን ይፈቀድለታል

ፕሮግራሞቻችን እና አገልግሎቶቻችን የሚፈቀዱት ለሚከተሉት ሰዎች ነው፦

- በስደተኝነት እና ዜግነት ህግ (አይኤንኤ) አንቀጽ 207 መሰረት እንደ ስደተኛ ወደ ዩኤስ እንዲገባ የተፈቀደለት
- በአይኤንኤ አንቀጽ 208 መሰረት ጥገኝነት የተፈቀደለት
- በ 45 ሲኤፍአር ክፍል 401 መጠይቅ መሰረት ከኩባ ወይም ከየሃይቲ የመጣ በውጭ ስራዎች፣
- ወደ ውጪ ላኪ ገንዘብ ድጋፍ፣ እና የተያያዙ ህጎች (Foreign Operations, Export Financing, and Related Appropriations Act) 1988 ክፍል 584 መሰረት ወደ ዩኤስ የገቡ ከቬትናም የመጡ አሜሬዥያኖች
- በዩኤስ የህጻናት እና ቤተሰቦች አስተዳደር የተረጋገጠ የህዝብ ድጋፍ እንዲቀበሉ የተፈቀደላቸው የሰው ዝውውር ከፉኛ ተጠቂዎች (ኤሲኤፍ)
- የኢራቅ ወይም የአፍጋን ልዩ ስደተኛ ቪዛ (ኤስአይቪ) የያዙ

## ለማመልከት ምን ያስፈልጋል

- በቤትዎ ካሉ ሁሉም ሰዎች የኢሚግሬሽን ሁኔታ ማስረጃ
- የመኖሪያ ማስረጃ
- የቤትዎ አጠቃላይ ገቢ (ከሁሉም አቅጣጫ)
- አመልካቹ ሁለተኛ ስደተኛ ከሆነ በሌላ ስቴት ጥቅማ ጥቅሙን መዘጋቱን ማስረጃ

### የስደተኛ የሽግግር የገንዘብ እርዳታ (አርቲሲኤ)

የፌዴራል መንግስቱ የሜሪላንድ ስቴት አርቲሲኤን እንዲያስተዳድር ሙሉ የገንዝብ ድጋፍ ያደርጋል። ፕሮግራሙ ተቀባዮች ስራ እስኪያገኙ ድረስ መሰረታዊ ወጭዎችን ለመሸፈን የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል። ፕሮግራሙ በጥቅማ ጥቅሞች እና መጠይቆች ከሜሪላንድ የጊዜያዊ የገንዝብ እርዳታ ለቤተሰቦች (ቲሲኤ) ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፣ የተቀረጸው ግን ለቲሲኤ ብቁ ላልሆኑ ብቁ ስድተኞች ነው።

### የስደተኛ የመጀመሪያ የጤና ምርመራ ፕሮግራም (አይአርኤችኤስ)

አዲስ የመጡ ስደተኞች የመጀመሪያ የጤና ምርመራ (አይአርኤችኤስ) ወደ ዩኤስ እንደመጡ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ የመልሶ ማስፈሪያ ኤጀንሲዎች ሃላፊነት ነው። የአይአርኤችኤስ ቀጠሮዎች አዲስ መጤዎች አስቸኳይ እርዳታ የሚያስፈልገው የጤና ሁኔታ እንዳለ ለማወቅ ይጠቅማሉ። እንዲሁም በአይአርኤችኤስ ህጻናት ለትምህርት ቤት ምዝገባ የሚጠየቀውን ክትባት ያገኛሉ። ከአይአርኤችኤስ በሁዋላ፣ ደንበኞች ለመከላከል ህክምና እና ለቀጣይ እንክብካቤ ወደ መጀመሪያ እንክብካቤ ሃኪም ይመራሉ።

### የስራ እርዳታ:

ለደንበኞች ራስን ማስቻል የስደተኛ መልሶ ማስፈሪያ ፕሮግራም አላማ ነው። የሚሳካውም ግለሰቦች እና ቤተሰቦች የመንግስት ድጋፍ የማያስፈልገው ኢኮኖሚያዊ ደህንነት ላይ ሲደርሱ ነው። ራስን መቻል የሚሳካው ለኢኮኖሚያዊ ጫና ለተጋለጡ ህዝቦች ላይ ያተኮሩ ሰፋት ባላቸው የህብረተሰብ እና የስራ አገልግሎቶች ነው። የተለያዩ ፕሮግራሞችን እና ስትራቴጂዎችን በመጠቀም፣ ኤምኦአርኤ ሰጭዎች ለያንዳንዱ ስደተኛ በተማከለ መልኩ የስራ አገልግሎቶችን ያቀርባሉ። በኤምኦአርኢ የሚደገፉ የስራ አገልግሎቶች ለምሳሌ ያህል እነዚህን ያጠቃልላሉ፦

- የስራ ዝግጁነት ስልጠና
- የስራና የትምህርት ማስረጃ ዝርዝር መጻፍ
- የስራ ፍለጋ ድጋፍ
- የሙያ ስልጠና
- የቃለ መጠይቅ ዝግጅት
- የመጓጓዣእርዳታ
- በቃለ መጠይቅ ወቅት ማስተርጎም
- ከቅጥር በሁዋላ ለሙያ ስኬት ክትትል

### እንግሊዝኛ ለሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች (ኢኤስኦኤል)

እንግሊዝኛ የሚናገሩ ስደተኞች የፈጠነ የህብረተሰብ መዋሃድ እና በኢኮኖሚ ራስን መቻል ስለሚያመጡ ስደተኞች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃታቸውን ማዳበር ለኤምኦአርኤ አላማ መሳካት ወሳኝ ነው። በኢኤስኦኤል ክፍሎቻችን አማካይነት፣ ተሳታፊዎቻችንን ለዜግነት ፈተና እናዘጋጃቸዋለን። ኤምኦአርኤ ነጻ የኢኤስኦኤል ክፍሎችን በመላው ስቴት ይሰጣል።